**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2019 ዓ.ም. የክረምት ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 005374**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የቃል መጽሐፍ ቅዱስ

ቤት፣ ትምህርትና ቤተሰብ — ለአዲስ ገቢዎች የቀረበ መጠይቅ

## ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. <u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. <u>የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎች ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — (4x16) — | 64 | ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት <u>ወይም</u>፦ ምዕራፍ ሦስት | — (3x12) — | 36 | ነጥብ |
| በአጠቃላይ | — | 100 | ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦
የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. <u>ልዩ መመሪያ</u>፦ የለም።

እንደ <u>ንድፍ</u> (<u>טיוטה</u>) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) <u>በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ</u>፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።
በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 005374**

**תרגום לאמהרית (6)**

# תורה שבעל פה

בית, חינוך ומשפחה — שאלון לעולים חדשים

## הוראות לנבחן

א. <u>משך הבחינה</u>: שעה וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | |
|---|---|---|
| פרק ראשון | —(16×4) — | 64 נקודות |
| פרק שני <u>או</u>: פרק שלישי | —(12×3) — | 36 נקודות |
| סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי־לועזי / לועזי־עברי.

ד. <u>הוראות מיוחדות</u>: אין.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).
רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה.
רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አራቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 16 ነጥብ)።

**1.** መሻት እና ውጤት / יצר ויצירה

ሀ. (1) በ"ራምባም" መሠረት በወንድ እና በሴት ጓደኛሞች መካከል የሚደረግ የፍቅር መነካካት (נגיעה של חיבה) የተከለከለ ነው።
ይህን መነካካት ሊቃውንት ለምን ከለከሉ?

(2) በተማርከው መሠረት፤ በወንድ እና በሴት ጓደኛሞች መካከል የሚደረግ የፍቅር መነካካት የተከለከለበትን ተጨማሪ ምክንያት ጻፍ።

(5 ነጥብ)

ለ. (1) የመገናኘት (דוחיי) መከልከል/እገዳ ምን እንደሆነ አብራራ እና ለዚህ እገዳ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ጻፍ።

(2) በሩ ለብዙሃን ክፍት በሆነ ክፍል የሚገኙ ሴት እና ወንድ የመገናኘት እገዳን አይተላለፉም። ለምን እንደሆነ አብራራ።

(11 ነጥብ)

**2.** "ኪዱሺን" እና ጋብቻ / קידושין ונישואין

ሀ. የ"ኪዱሺን" ምስክሮች በ"ኪዱሺን" ሰዓት ልብ ሊሏቸው የሚገባቸው / የሚያስፈልጓቸው ሁለት ድርጊቶች አሉ።
እነዚህን ሁለት ድርጊቶች ጥቀስ። (5 ነጥብ)

ለ. ከ"ሑፓ" በኋላ ሙሽራዋ ራስዋን የምትሸፍንበትን (כיסוי ראש) በተመለከተ ሁለት ልማዶችን ጻፍ።
(4 ነጥብ)

ሐ. (1) በራባናት ባልሆነ ጋብቻ (נישואים אזרחיים) የተጋቡ ጥንዶች ባለትዳር ናቸው ብለው የሚያስቡ የሕግ ሰዎች አሉ።
ለዚህ አመለካከት አንድ ማሳመኛ ጻፍ።

(2) በራባናት ባልሆነ ጋብቻ የተጋቡ ጥንዶች ባለትዳር እንደሆኑ የማያስቡ የሕግ ሰዎች አሉ።
ለዚህ አመለካከት አንድ ማሳመኛ ጻፍ።

(7 ነጥብ)

**3.** ባልና ሚስት አንዳቸው ለአንዳቸው ያሉባቸው ግዴታዎች / מחויבויות שבין איש לאשתו

ሀ. በጋብቻ ውል ("כתובה") ባል ለሚስቱ ሁለት ሁኔታዎችን በተመለከተ ያለበት ግዴታዎች ተመዝግበዋል።

(1) እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

(2) ከሁለቱ ሁኔታዎች ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ግዴታዎችን ጻፍ።

(8 ነጥብ)

ለ. (1) "ክቱባ"ው ሰው ሚስቱን እንዳያባርር እንዴት እንደሚከለክለው አብራራ።

(2) "ተጨማሪ ክቱባ" ("תוספת כתובה") ምንድን ነው? ሊቃውንት ይህንን ተጨማሪ ለምን ደነገጉ/ አወጡ? (8 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

4. የቤት አሠራር / בניית הבית

א. (1) የሰንበት ሻማ ማብራት ለቤት ሰላም እንዴት እንደሚረዳ አብራራ።

(2) የሰንበት ሻማ እና የ"ሃኑካ" ሻማ ለመግዛት ገንዘብ የሌለው ድሃ ሰው — የትኛውን ሻማ ነው መግዛት ያለበት? ለምን እንደሆነ አብራራ።

(6 ነጥብ)

ב. "כי יקח איש אִשה חדשה... נקי יהיה לביתו שנה אחת ושִׂמח את אשתו אשר לקח" (דברים, כ"ד, ה').

(1) "נקי יהיה לביתו" የሚለውን ትዕዛዝ እንዴት መፈጸም እንደሚቻል ጻፍ።

(2) "שנה אחת" ለሚሉት ቃላት የራባን ሞሼ ጽቪ ነሪያን ጥያቄ ጻፍ እና መልሱን አብራራ።

(10 ነጥብ)

5. መፋታት / גירושין

א. መፋታትን በተመለከተ የራባን ጌርሾም ሕግ ምንድን ነው? ይህን ሕግ የደነገገው ለምንድን ነው?

(6 ነጥብ)

ב. "היתר מאה רבנים" ምንድን ነው? በዚህ ፈቃድ የሚጠቀሙትስ በየትኛው ሁኔታ ነው?

(5 ነጥብ)

ג. በእስራኤል አገር ሕግ መሠረት፤ ሚስቱን መፍታት ኖሮበት እምቢተኛ ለሚሆን (סרבן גט) ወንድ ሊጣሉበት የሚችሉ ሦስት ማዕቀቦችን (סנקציות) ጻፍ።

(5 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

**በተማርካቸው ይዘቶች መሠረት ምዕራፍ ሁለትን ወይም ምዕራፍ ሦስትን መመለስ አለብህ።**

## ምዕራፍ ሁለት (36 ነጥብ)

**ከመጽሐቱ ላይ ከ'א - א"' ያሉትን ምዕራፎች ተምረህ** ከሆነ ከ6-9 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

**6.** ጥንድነትና ትዕዛዛት "ብዙ ተባዙ" / "פרו ורבו" זוגיות ומצוות

**አ.** በራብ ኤሊያሁ ዴስሌር መሠረት፥ በጥንዶች መካከል የፍቅር መንስኤው ምን እንደሆነ አብራራ። (6 ነጥብ)

**በ.** የመብዛት እና መባዛትን ትዕዛዝ ምክንያት (טעם למצוות פרייה ורבייה) አብራራ። (6 ነጥብ)

**7.** መርገም እና መጥራት / טומאה וטהרה

**አ.** የእስራኤል ሴቶች ልጆች በራሳቸው ላይ አጠበቁና የመርገምን ፍርድ (דין הנידה) ከመርከስ ፍርድ (דין הזבה) ጋር እኩል አድርገውታል።
ለዚህ ማጥበቅ አንድ ምክንያት ጻፍ። (4 ነጥብ)

**በ.** (1) "ואל אִשָּׁה בְּנִדַּת טֻמְאָתָהּ לֹא תִקְרַב לְגַלּוֹת עֶרְוָתָהּ".
"לא תקרב" በሚለው ትዕዛዝ የተጠቃለሉ ሁለት እገዳዎችን ጻፍ።

(2) በመርገም ቀን ካለች ሴት ጋር የመገናኘት እገዳ (איסור לחיות חיי אישות) በ"ቶራ" እህት ማግባት ከታገደበት አጠገብ ተጽፏል።
ከዚህ መቀራረብ ምን መማር ይቻላል?
(8 ነጥብ)

**8.** ሻሽ ማሰር (ራስ መሸፈን)

**አ.** (1) "דת משה" ምንድን ነው? በ"דת משה" መሠረት የታዘዘው የራስ መሸፈኛ ምንድን ነው?
(2) "דת יהודית" ምንድን ነው? በ"דת יהודית" መሠረት የታዘዘው የራስ መሸፈኛ ምንድን ነው?
(9 ነጥብ)

**በ.** ሴት በቤቷ ራሷን የመሸፈን ግዴታ የሌለባት በየትኛዎቹ ሁኔታዎች ነው? (3 ነጥብ)

**9.** አጫጭር ጥያቄዎች

ከአ-ד ካሉት ንዑሳን ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ። (ለእያንዳንዱ ንዑስ ጥያቄ – 4 ነጥብ)።

**አ.** "הרהורי עֲבֵרה קשים מעֲבֵרה" ለምንድን ነው?

**በ.** ሴት ለምንድን ነው ይልቁንም በቀለበት የምትቀደሰው? ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ጻፍ።

**ገ.** በባልና ሚስት መካከል ባለ ግንኙነት ጉዳይ ላይ "שאלת רב"ን ለምንድን ነው ይልቁንም ጠያቂውን በቅርብ ወደ ሚያውቀው ራባን ማቅረብ አስፈላጊ የሆነው?

**ד.** "אישה עגונה" ማን እንደሆነች አብራራ እና ሴትን ካልተፈታችበት (מעגינותה) ማላቀቅ ዓላማው የሆነ አንድ ከ"ሃላኻ" ምሳሌ ጻፍ።

/ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል/

**በተማርካቸው ይዘቶች መሠረት ምዕራፍ ሁለትን ወይም ምዕራፍ ሦስትን መመለስ አለብህ።**

## ምዕራፍ ሦስት (36 ነጥብ)

**ከመጽሐፉ ላይ ከ'א - 'ו , ከ'' - ד'' ያሉትን ምዕራፎች ተምረህ** ከሆነ ከ10-13 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

**10.** ጥንድነትና ትዕዛዛት "ብዙ ተባዙ" / "פרו ורבו" זוגיות ומצוות

א. በራብ ኤሊያሁ ዴስሌር መሠረት፣ በጥንዶች መካከል የፍቅር መንስኤው ምን እንደሆነ አብራራ። (6 ነጥብ)

ב. የመብዛት እና መባዛትን ትዕዛዝ ምክንያት (טעם למצוות פרייה ורבייה) አብራራ።። (6 ነጥብ)

**11.** የቤተሰብ አኗኗር / התנהלותה של משפחה

א. (1) የጋድ ልጆች እና የሮቤል ልጆች ከንብረት እና ከቤተሰብ ቅድሚያ የሚሰጡት ለየትኛው ነበር?
(2) በሞሼ ራቤኑ መሠረት ቅድሚያ የሚሰጠው ምንድን ነው?
(5 ነጥብ)

ב. በዛሬው ጊዜ ብዙ ሴቶች ቤተሰብን በገንዘብ በመደገፍ ላይ ተሳታፊዎች ናቸው።
በቤተሰብ ሕይወት መምራት እና በገንዘብ በመደገፍ መካከል የሚመከረው ጥምረት ምንድን ነው?
በመልስህ ላይ የቤተሰብ እናት ያላትን ሁለት የሕይወት ወቅቶች ጥቀስ። (7 ነጥብ)

**12.** መርገም እና መጥራት / טומאה וטהרה

א. የእስራኤል ሴቶች ልጆች በራሳቸው ላይ አጠበቁና የመርገምን ፍርድ (דין הנידה) ከመርከስ ፍርድ (דין הזבה) ጋር እኩል አድርገውታል።
ለዚህ ማጥበቅ አንድ ምክንያት ጻፍ። (4 ነጥብ)

ב. (1) ."ואל אִשה בְּנִדַּת טֻמאתה לא תִקְרַב לגלות עֶרְוָתָהּ"
"לא תקרב" በሚለው ትዕዛዝ የሚጠቃለሉ ሁለት እገዳዎችን ጻፍ።
(2) በመርገም ቀን ካለች ሴት ጋር የመገናኘት እገዳ (איסור לחיות חיי אישות) በ"ቶራ" እህት ማግባት ከታገደበት አጠገብ ተጽፏል።
ከዚህ መቀራረብ ምን መማር ይቻላል?
(8 ነጥብ)

**13.** አጫጭር ጥያቄዎች

ከא-ד ካሉት ንዑሳን ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ። (እያንዳንዱ ንዑስ ጥያቄ – 4 ነጥብ)።

א. ሴት ለምንድን ነው ይልቁንም በቀለበት የምትቀደሰው? ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ጻፍ።

ב. "אישה עגונה" ማን እንደሆነች አብራራ እና ሴትን ካልተፈታችበት (מעגינותה) ማላቀቅ ዓላማው የሆነ አንድ ከ"ሃላኻ" ምሳሌ ጻፍ።

ג. ሰው የገንዘብ ወጪውን መቀነስ እና ማባከን መተው አለበት። ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ጻፍ።

ד. በባልና ሚስት መካከል ባለ ግንኙነት ጉዳይ ላይ "שאלת רב"ን ለምንድን ነው ይልቁንም ጠያቂውን በቅርብ ወደሚያውቀው ራባን ማቅረብ አስፈላጊ የሆነው?

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך